# ቅኔ።

ቅኔ ያማርሽ ቃል ቃና ለዛ ያለሽ፤

አንቺም ተናገሪ ስንትርጉም እንዳለሽ።

ቅኔ የኛ ቅን፤

ቅንነትሽን አየን፤

ባለ ሁለት ትርጉም፤

ውቢቱ ስልምልም፤

ደግሞ ሲያስፈልግሽ፤

ውልግድ ጥምም ያልሽ።

ቆፍሮ ካልሆነ ማንም አያወጣሽ፤

ተጣመሽ መውጣትሽን ዳግም እያሳየሽ

የቂም መወጫነት ክህኖትም አለሽ፤

ከቶም አትረቺ ጊዜ ሲበድልሽ

ሰምና ወርግ ነው ለዛና ጣእምሽ።

አይ የኛ ሽጊቱ የሚከስሽ የለም፤

እሰከነ አካቴውም ለፈርድ አትመቺም።

ባለቅኔ ጠፍቶ ወይስ አንቺ ጠፋሽ

ታዲያ ለምንዴር ነው ዝም ችጭጭ ማለትሽ

አንቺም ተሟገቺ አደራ አለብሽ

ባፈና ተይዘሽ ከእስር አሰገቡሽ?

ነጭ ጥቁር ሆነሽ ሙሽርሽር ብለሽ

ያየሽውን ሁሉ ቀምረሽ ቀማምረሽ

የታሰረን ሁሉ መላ መላ ብልሽ፤

ጊዜ ስታገኚ አንችም ትፈቻለሽ።

አማርሽ ፎነጋሽ

ቀናሽም ጠመምሽ

አንችንም በተራሽ

ቅን ቅኔ እንበልሽ።

ገበያ የመውጫ ሽመታ ደረሰ፤

የሚገዛ ጠፍቶ ባዶ ተመለሰ።

ቁመቱም ያጠረ ከአይኑ ፈጣጣ፡

እንዲያው ለነገሩ ከሥራው መላጣ።

ሕዝቡንም አመሰው መልሶ ቀልሶ፤

ካገሩ ነጎደ ብረት ወርቅ ለብሶ።

የማያልፍ መስሎት ጊዜም እንደባቡር፤

ተግባሩ በመላ የተንኮል የቁማር።

ጠማማ ሞላና ባገር በወገኔ፤

እኔማ ምኞቴ ወይ ቅኔ ወይቅኔ።

ተራኮተ አሉ ወገን በየፊናው፤

ጠላትም ሳይነካው ቅን ቅን እየበላው።

በጊዜ ነግረናል ገና በጥዋት፤

መላ አገሪቱን የቀን ጅብ ሳይበላት፤

እንደ ሙዳ ስጋ ለቅርጫ ሳይበልት።

ያአባትህ አገር ያእናትህ አገር፤

የቀደሙት አገር የጀግኖቹ ምድር፤

ቅርጫውን ሲዶልት ገና ሳትበለት፡

ተነሳ መክተው ይሂንን ባንድነት።

ፖለቲክ ነጎደ ጭቅጭቅ ገደደ፤

ሕዝባችን አለቀ በረሃም ነደደ።

አትንኩዋት በነገር ከቶ እንዳይብስባት፣

ታማ ተኝታለች ያለችን አንድናት።

ነገሩ ቢበዛ ደግሞ ቢደጋገም፣

ለማንም እንዳይበጅ ለጠላትም አይጥም።

ዘመን ተከበር ሚሊኔም ደረሰ፣

እህልና ቅምመ ሽመታ ቀለሰ፣

ላውዳመት መዋያ ብሩን አፈሰሰ፣

ገበያ ወጣና ባዶ ተመለሰ።

እውነት ጠፋችና ድህን ለመኮነን፣

የሚወራን ሁሉ ከንቱ ነው ምናምን::

ማጣጣም ካቃተው ያገርን ምንነት፣

መገመት ካቃተው መጪውንም መአት፣

አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የቀለመባት፣

ለዘመን የቆየች ጊዜ የማይሽራት፡

ካሁኑ ንገሩት ባንዴራ አንድ ናት፡፡

ካዝናው ባዶ ሆነ ወርቁንመም ጨምሮ፣

ተዘረፈ ንብረት ችብቸባውም ንሮ፣

ምንም አልቀረላት ለዚያች ለአገሬ፣

ተሰለበች አሉ ዘንድሮስ ሺብሬ፡፡

ሰላም እንደምን ነሽ ለውሎ ላዳርሽ

የመከራ ቀንበር አንችም ተጫነብሽ

መሽጥ መለወጡ እየባስ ሲንር፣

ሰው እንዲህ ይራባል በሞላበት ሽብር።

ጠማማው በርክቶ ቀጥ ያለ ሲታጣ፣

ርክሰት ሁሉ በዝቶ እውነት ስትበጣ፣

መጪው እንዲያምርልን ጸሐይ እንድትወጣ፤
ላገሩ ለሕዝቡ አባት ሆይ ቀናውጣ።

ምክር ተቀበሉ ትገሳጽን በቅጡ፤
ስሙና ተስማሙ መልካም መላን አምጡ፤
እንዲሆን በሕብረት በጊዜ ለለውጡ፤
በከንቱ ከሚያምስ ልጥፍን አትጡ።

አንተም በበኩልህ በግብረ ሰነይህ፤
የምትወክለውን ሳትፈራ ከሀቅህ፤
መርጠህ ተመራርጠህ መሪህም እንዲሆን፤
ለሰው እንዲበጀው አባትም መላኩን።

ካሁኑ በወቅቱ አስላና ቀምረው፤
ሁዋላ ከመጣደፍ ዳር መሀል ሲናጋው፤
መልካሙን እምርተህ ትርፍህንም አቅጥ፡
መጣደፍ ሆኖብህ እራስን ከመናጥ።

ሰም ለበስ ቅጥለበስ አሁን ምነ ያደርካል፤
ቃላትን መደርድረ ለምኑ ይጠቅማል፤
ሕዝቡ በያለበት በአይነት ይታመሳል፤
ሰላም ተንቃለች ብረት ለበስ ይላል።

በአዲሱ ትውልድ በዚህ በኛ ዘመን፤
አገር ሳትበተን ተወቃሽ ሳንሆን፤
ነገር ንግግርን እንዲሆን በማጤን፤
በማስተዋል ሁሉን አብረን ተነባብረን፤
ከማአት ለመትረፍ መማጸን አለብን፤
አድነን እያልን ከክፉ ሰውረን፤
አባትም ከሰማይ ከመከራ አውጣን።

**ፍሬው አንተነህ**

05/102012